## ይመጣል ተብሎ የሚጠበቀው አንተ ነህ"? ማቴ 11፡1-6-15

ማቴ 11፡1-10፣ መጥምቁ ዮሐንስ በዮሐ 1፡26-36-41፣ ማር 1፡1-9-11፣ ባለው ክፍል ጌታ ኢየሱስ መሲሁ ነው ብሎ የመሰከረ የመጀመሪያው ሰው ሆኖ ሳለ ሄሮድስ እስር ቤት አሰገብቶት መከራ በመቀበል ላይ ስለ ነበር ጌታ ኢየሱስ መሲሁ መሆኑን የተጠራጠረ ይመስላል፣ "ይመጣል ተብሎ የሚጠበቀው አንተ ነህ? ወይስ ሌላ እንጠብቅ?" ሲል ጠየቀ። " ማቴ 11÷3፡፡ ምናልባት ኢየሱስ የሚመጣው መሲሁ ቢሆን ኖሮ ጌታ ያከናውነው የነበረውን መንፈሳዊ ሥራ የሚያከናውን ሳይሆን እስራኤልን ከሮማዊያን ቅኝ ተገዢነት ነጻ በማውጣት ፖለቲካዊ ሥራ የሚሰራና ያለ አግባብ እስር ቤት ተጥዬ ያለሁትን እኔን ከእስር ቤት ያስፈታኝ ነበር ብሎ ስላሰበ ሊሆን ይችላል፡፡

ጌታ ኢየሱስ ለመጥምቁ ዮሐንስ መልዕክተኞች የሰጠው መልስ እርሱ ያከናውነው የነበረው ሥራ ትክክለኛ የመጣበትን የመሲህነት ዓላማ የሚገልጥ ተግባር በማከናወን ላይ መሆኑን የሚያሳይ ነበር፡፡ እየሰራ ያለውም ሥራ ዝርዝር፤ "ዕውሮች ያያሉ፤ አንካሶች ይራመዳሉ፤ ለምጻሞች ይነጻሉ፤ ደንቆሮዎች ይሰማሉ፤ ሙታን ይነሳሉ፤ ለድኾችም የምሥራች እየተሰበከ ነው፤" በማለት ዘረዘረለት፡፡ ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ያደርግ የነበረው የጠቀሳቸውን ተግባራት ብቻ ሳይሆን፣ መናገር የተሳናቸውን፣ ምርኮኞችን ነጻ ማውጣት፣ የአጋንንት እስረኞችንም መፍታት፣ ሽባዎችን ማበርታት…ምንም ዓይነት የጤንነት መጓደልና መንፈሳዊ ችግር ያለበት ሰው እርሱ ጋ መጥቶ ከችግሩ ሳይላቀቅ የተመለሰ አልነበረም፡፡ ስለዚህ በአሁኑም ዘመን ቢሆን ጌታ በሥራ ላይ ስለሆነ ማንኛውም ዓይነት የጤንነትና መንፈሳዊ ችግሮች ያሉበት አማኝ ጉዳዩን በጽኑ ዕምነት በጌታ ፊት ማቅረብና ፈጥኖ መፍትሔ ካላገኘም የጌታ ጉብኝት መምጣቱ ስለማይቀር ታግሶ በእምነት መጠበቅ ነው፡፡

ለመጥምቁ ዮሐንስ የላከለት መልስ ማጠቃለያው፣ "በእኔ የማይሰናከልም ብፁዕ ነው።" የሚል ነበር፡፡ ይህ ማጠቃለያ በጣም ወሳኝ የሆነ ጠቀሜታ ያለው ነው፡፡ ኀጢአትና ክፉ መናፍስት በሰው ዘር ላይ ያስከተሉትና ለሚያስከትሉት ማንኛውም ቀንበርና ሰቆቃ መዳኛ በጌታ ኢየሱስ ካልሆነ በስተቀር እግዚአብሔር የሰጠው ሌላ መፍትሔ ስለሌለ በማንኛውም ምክንያት በጌታ ኢየሱስ ከማመን በመራቅ መሰናከል መጨረሻው እጅግ አደገኛ ነው፡፡

ቀጥሎም እዚያ አብረውት ለነበሩት ሕዝብ ስለ መጥምቁ ዮሐንስ እስከዚያ ጊዜ ድረስ ከተወለዱት ነቢያት ሁሉ የሚበልጥና ለመሲሁ መገለጥ መንገድ ጠራጊ/የሚያመቻች ሰው ተብሎ ትንቢት የተነገረለት እርሱ መሆኑን ገለጠላቸው፡፡

ማቴ 11÷11፣ "እውነት እላችኋለሁ፤ ከሴት ከተወለዱት መካከል እንደ መጥምቁ ዮሐንስ ያለ አልተነሣም፤ ሆኖም በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ የሚያንሰው ይበልጠዋል።"

ጌታ ኢየሱስ መጥምቁ ዮሐንስ ከብሉይ ኪዳን ነቢያት ሁሉ የሚበልጥና ነብዩ ኤልያስ ተመልሶ ይመጣል የተባለለትም እርሱ መሆኑን ቢነግራቸውም ከአዲስ ኪዳን አማኞች ጋር ሲነጻጸር ግን ትንሽ የሚባለው በጌታ ኢየሱስ ያመነ ሰው እንኳ ከመጥምቁ ዮሐንስ

የሚበልጥ መሆኑን አስረድቷል፡፡ ምክንያቱም የአዲስ ኪዳን ዘመን የጀመረው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሰው ልጆች ኃጢአት መስቀል ላይ ተሰቅሎ ደሙን በማፍሰስ ሞቶ ከተነሳበት ጊዜ ጀምሮ ሰለሆነ መጥምቁ ዮሐንስ የሞተው የአዲስ ኪዳን ዘመን ከመጀመሩ በፊት በመሆኑ የጌታ ኢየሱስ ሞትና ትንሳዔ የሚያስገኘውን በረከት መውረስ ስለማይችል ነው፡፡ 2ቆሮ 3፡6፣ ዕብ 8፡6-13፤

**ማስታወሻ**፡- በሚልክያስ 4፡5 ላይ፣ "እነሆ ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ከመምጣቱ በፊት ነቢዩ ኤልያስን እልክላችኋለሁ፡፡" የሚል ትንቢት ተነግሮ ነበር፡፡ ማቴ 17፡10-13፣ ላይ ደቀ-መዛሙርቱ፣ "ታዲያ የኦሪት ሕግ መምህራን ከመሲሁ በፊት ኤልያስ አስቀድሞ መምጣት አለበት የሚሉት ለምንድን ነው?" ብለው ጠየቁት፡፡ "... ነገር ግን እላችኋለሁ፤ ኤልያስ መጥቷል፤ ሆኖም የፈለጉትን አደረጉበት እንጂ አላወቁትም፤" አላቸው፡፡ "በዚህ ጊዜ ደቀ-መዛሙርቱ ኢየሱስ የነገራቸው ስለ መጥምቁ ዮሐንስ መሆኑን ተረዱ፡፡" (ማር 9፡11-13)
ሉቃ 1፡17፣ "የአባቶችን ልብ ወደ ልጆቻቸው፣ የማይታዘዙትንም ወደ ጻድቃን ጥበብ ይመልስ ዘንድ፣ ለጌታ የተገባ ሕዝብ ለማዘጋጀት በኤልያስ መንፈስና ኀይል በጌታ ፊት ይሄዳል።" ስለሚል ኤልያስ ራሱ ከመቃብር ተነስቶ በመምጣት መጥምቁ ዮሐንስ ሆኖ ተወለደ ማለት ሳይሆን፣ በኤልያስ መንፈስና ኀይል በጌታ ፊት ይሄዳል ለማለት ነው፡፡

አይሁዶች መጥምቁ ዮሐንስን "አንተ መሲሁ ነህን?" ቀጥለውም ኤልያስ ነህን? ብለው ሲጠይቁት የሰጠው መልስ፤ ዮሐ 1፡20፣ 21፤ ከመመስከርም ወደ ኋላ አላለም፤ "እኔ ክርስቶስ አይደለሁም" ብሎ በግልጽ መሰከረ። [21] እነርሱም፣ "ታዲያ አንተ ማን ነህ? ኤልያስ ነህ?" ብለው ጠየቁት። እርሱም፣ "አይደለሁም" አለ። እነርሱም፣ "ታዲያ ነቢዩ ነህ?" አሉት። እርሱም፣ "አይደለሁም" ሲል መለሰ። የእርሱ መልስ ከላይ ጌታ ኢየሱስ ከተናገረው ጋር የሚቃረን ሊመስል ይችላል፡፡

ነብዩ ኤልያስና መጥምቁ ዮሐንስ በተለያየ ዘመን የኖሩ የተለያዩ ሰዎች ናቸው፡፡ ጌታ ኢየሱስ በሁለቱም ሰዎች ላይ የሰራው መንፈስና ኀይል ግን አንድ መሆኑን ተናግሯል፡፡ ይሄንን መጥምቁ ዮሐንስ በጌታ ካልተነገረው በስተቀር ላያውቀው ስለሚችል ነው ኤልያስ አይደለሁም ያለው፡፡

***ማቴ 11፥12፣ "ከመጥምቁ ዮሐንስ ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ መንግሥተ ሰማይ በብዙ ትገፋለች፤ የሚያገኟትም ብርቱዎች ናቸው፤"***

ጌታ ኢየሱስ ከዚህ ከፍ ብሎ ያለውን ጥቅስ በመናገር ሊገልጽ የፈለገው ጌታ ኢየሱስ ካስተማረበት ጊዜ ጀምሮ የወንጌሉ ቃል ሥራ በሚከናወንበት ስፍራ ሁሉ ብርቱ መንፈሳዊ ውጊያ ያለበት መሆኑንና በጉልበት ሳይሆን በእምነታቸው ብርቱዎች/ጠንካራ የሆኑ ሰዎች የወንጌሉን ቃል ተቀብለው በሚደርስባቸው የተለያየ ፈተና ጸንተው መቆየት የሚችሉት ብቻ በረከቱን ይወርሱታል ማለቱ ነው፡፡

ማቴ 11÷19፣ "የሰው ልጅ እየበላና እየጠጣ መጣ፤ እነርሱም፣ 'በልቶ የማይጠግብ፣ ጠጪ እንዲሁም የቀረጥ ሰብሳቢዎችና የኀጢአተኞች ወዳጅ' አሉት። **ጥበብ ግን በሥራዋ ጸደቀች።"** ሲል ጠቢብ ሰው ጥበበኛ መሆኑን የሚረጋገጠው ሰርቶ በሚያሳየው የጥበብ ሥራው ነው የሚል ነበር፡፡

ከአዳም ዘመን ጀምሮ እግዚአብሔር በሰጠው የተስፋ ቃል መሰረት መጥምቁ ዮሐንስ ይህን ጥያቄ ወደ ጌታ ኢየሱስ እስከ ላከበት ጊዜ ድረስ በተለይም በአብርሐም ዘር በእስራኤል ምድር ይመጣል ተብሎ የሚጠበቅ የሰው ዘር በኃጢአት ምክንያት ከደረሰበት መንፈሳዊ ውድቀትና መዘዙ ሁሉ የሚያስመልጥ አዳኝ ነበር፡፡

ቃሉ "ይመጣል ተብሎ የሚጠበቀው" ነው እንጂ፣ "ይመጣሉ ተብሎ የሚጠበቁት" ስለማይል ይመጣል ተብሎ የሚጠበቀውና እግዚአብሔርም ይመጣል ያለው ብዙ ቁጥር ያለው ሳይሆን አንድ ብቻ ስለ ነበር ነው፡፡

ደግሞም "ይመጣል ተብሎ የሚጠበቀው" ሲል፣ መምጣቱን የሚጠባበቁት ሴቴ ጾታ ያላት (ትመጣለች) ሳይሆን ወንዴ ጾታ ያለውን መሆኑን ያሳያል፡፡

ይመጣል ተብሎ የሚጠበቀው መሲህ እኔ ነኝ፡፡ እነሆ መጥቻለሁ ብሎ የተናገረና ይሄ ቃሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ የሚገኝ ከጌታ ኢየሱስ በስተቀር ሌላ ማን የለም፡፡

ጌታ ኢየሱስ ከመጣ በኋላ የምስራቹን ቃል እየሰበከ በእኔ እመኑ በእኔ ካላመናችሁ በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ ብሎ ያለና በመጽሐፍ ቅዱስ ይሄ ቃሉ የሰፈረ ከጌታ ኢየሱስ ሌላ ማንም የለም፡፡

ጌታ ኢየሱስ የአግዚአብሔርን መንግስት እየሰበከ እኔን ተከተሉኝ፣ ሕዝቦችም ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ተከታዮቼ (ደቀ_መዛሙርቴ) አድርጓቸው ብሎ እንዳዘዘው፣ የተናገረ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ሰፍሮለት የሚገኝ ሌላ ማንም የለም፡፡

ከአዳም ዘመን ጀምሮ ብዙ ታዋቂ ሰዎች ነቢያት፣ ሊቀ-ካህናትና ካናት፣ ነገስታትም፤ ጀግና የጦር አለቆችም፣ ጻድቃንም መጥተዋል/ተወልደዋል፣ ነበሩም፣ ተራ በተራ ሲመጡ ይመጣል የተባለው ይሄ ይሆን ወይ ተብለው ይታሰቡ ነበር፡፡ ነገር ግን ማናቸውም ይመጣል ተብሎ የሚጠበቀው እኔ ነኝ አላሉም፣ ይመጣል የተባለው መሲህ ሲመጣ ያደርጋቸዋል ተብለው የተነገሩ ማረጋገጫ/ማስረጃ/ እርሱነቱን ለይተው የሚያሳዩ ምልክቶች/ተግባራት ሲያከናውኑ አልተገኙም/ አልታዩም፡፡ ለሰው ዘር መንፈሳዊ ውድቀት መፍትሔ ሊያስገኙ ሕልሙም እንዳላቸው አልተናገሩም፡፡

ጌታ ኢየሱስ፣ ሐዋሪያትን በዓለም ሁሉ ሂዳችሁ ሰዎችን ተከታዮቼ አድርጓቸው ነው እንጂ ተከታዮቻችሁ ወይም የሌሎች ቅዱሳን ተከታዮች አድርጓቸው አላለም፡፡ በአሁኑ ዘመን ብዙ ሕዝብ እየተከተለ ያለው ተከተሉኝ፣ በእኔም እመኑ ያላሉትን፣ መጽሐፍ ቅዱስም ተከተሉዋቸው ያላለውን ነው፡፡ ከዚህም በላይ በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር

ሕዝብ በአንድ ስፍራ (ዘዳ 6፥13) በእግዚአብሔር ስም እንዲምል ታዞ ነበር፡፡ በአዲስ ኪዳን ግን መሃላ ፈጽሞ መከልከሉን የሚያሳዩ ጥቅሶች ብዙ ናቸው፡፡

ለምሳሌ፡- ያዕቆብ 5፡12 “ወንድሞቼ ሆይ! ከሁሉም በላይ በሰማይ ወይም በምድር ወይም በሌላ በምንም ነገር አትማሉ፤ ንግግራችሁ አዎን ከሆነ በእውነት አዎ ይሁን፤ አይደለም ከሆነም በእውነት አይደለም ይሁን፤ እንዲህ ካልሆነ ግን ይፈረድባችኋል።” ይላል

ስለዚህ በፍጥረታት ስም የሚደረግ መሃላ ፍርድ (ቅጣት) የሚያስከትል መሆኑ የእግዚአብሔር ቃል እየተናገረ ክርስቲያን ነን የሚሉ ሰዎች እንዲያውም ከእግዚያብሔር ስም ወጪ በፈለጋቸው ፍጥረት ሲምሉ ምንም ቅር አይላቸውም፤ ተዉ እንዲህ አይደረግም የሚላቸውም መሪም የላቸውም፡፡

ቅዱሳን የእግዚአብሔር መላእክትም ከእግዚአብሔር አምላክ ዘንድ ወደ ሰው ልጆች ተልከው በተለያዩ ጊዜያት መጥተዋል፣ በምድር ላይም የሚኖሩም ነበሩ፣ አሁንም አሉ፡፡ ግን ከእነዚህ ማናቸውም በሰው ዘር ላይ ኃጢአት ያስከተለውን ውድቀትና ውስብስብ ችግር እልባት ሊሰጡት አልቻሉም/አልሰጡትም፣ እንዲህ ዓይነት ኃላፊነት ከእግዚአብሔርም አልተሰጣቸውም፡፡

መሲሁ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዓለም በመምጣቱ ምክንያት ለተለያየ ተግባርና አገልግሎት እግዚአብሔር ብዙ ሰዎችና መላዕክትን ተጠቅሟል፡፡ በአሁኑ ዘመን እነዚህ እግዚአብሔር መሲሁን ለማስተዋወቅ የተጠቀማቸውን ስማቸው እየተጠራና ስራቸው እየተወሳ ያለው በእርሱ መምጣትና መጥቶም በሰራው ሥራ አማካይነት ብቻ ነው፡፡ አለዚያ የአሁን ትውልድ የዚያን ዘመን እስራኤላዊያን ሰዎች ሁሉ እንደ ማያውቅ ስማቸው እንኳ አይታወቀንም ነበር፡፡ እነዚያም ሁሉ እግዚአብሔር ለተጠቀማቸው አግለግሎት የበቁት እግዚአብሔር በጸጋው ስለመረጣቸው ነው እንጂ በራሳቸው ብቃት ወይም ፍጹምነት ስለተገኘባቸው አይደለም ወይም የሰጡት አገልግሎት እነርሱ ሊያገለግሉበት ያቀዱት ዕቅድ የነበራቸው ሆኖ አይደለም፡፡ (1ቆሮ1፡26-31)

ይህ ማለት ግን በተለይ የጌታ ኢየሱስ ቤተሰቦችና ሐዋሪያት ከተለወጡ በኋላ ለጌታ ሲሉ የነበራቸውን ቤትና ንብረት ሁሉ በመተው ሕይወታቸውን በመሰዋት ጭምር ለወንጌል የከፈሉት ዋጋ በጣም ከፍተኛ መሆኑን ባለመካድ ነው፡፡ ለዚያ አርዓያነት ላለው ተግባራቸው ተገቢውን ወሮታ የሚከፍላቸው እግዚአብሔር ነው፡፡

ሉቃስ 3፡15-16 "በዚያን ዘመን ሕዝቡ ሁሉ የመሲሁን መምጣት በጉጉት ይጠባበቅ ነበር፡
፡ ስለዚህ መጥምቁ ዮሐንስን "ይህ ሰው ምናልባት መሲሁ ይሆንን?" እያሉ ያስቡ ነበር፡፡
16 ዮሐንስ ግን ለሁሉም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ “እኔ በውሃ አጠምቃችኋለሁ፤ ነገር ግን
ከእኔ የሚበረታ ይመጣል፤ እኔም የእርሱን የጫማ ማሰሪያ መፍታት የሚገባኝ
አይደለሁም፤ እርሱ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል፤" በማለት መስክሯል፡፡

በመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት ዘመን ብቻ ሳይሆን ከዚያ በፊትም ለብዙ ዘመናት በተመሳሳይ ሁኔታ የመሲሁ መምጣት ይጠባበቁ እንደነበር ጌታ ኢየሱስ እንዲህ ሲል ገልጾታል፡፡

ማቴዎስ 13፥17 “እውነት እላችኋለሁ፤ ብዙ ነቢያትና ብዙ ጻድቃን እናንተ የምታዩትን ለማየትና የምትሰሙትንም ለመስማት ተመኝተው ነበር፤ ግን አልሆነላቸውም።” (1ጴጥ 1፡10-12)

መጥምቁ ዮሐንስ (የብሉይ ኪዳን የመጨረሻው ነብይ የነበረው) ራሱ መሲሁ የሆነው የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግደው የእግዚአብሔር በግ መምጣቱን አውቆ ይኸውና ብሎ ለተከታዮቹ በማሳየት መስክሮ ነበር፡፡ ነገር ግን መጥምቁ ዮሐንስ የጊዜው ንጉስን ሳይቀር ማንንም ሳይፈራ ከኃጢአት ተመለሱ ብሎ በማስጠንቀቁ መከራ እየተቀበለ ባለበት ሰዓት ኢየሱስ ያደርጋቸው የነበሩ ነገሮች በሰማ ጊዜ ወደ ኢየሱስ ይመጣል ተብሎ የሚጠበቀው አንተ ነህን ወይስ ሌላ እንጠብቅ ሲል መልዕክተኞች ላከበት፡፡ ጌታ ኢየሱስም ከ ማቴ 11፡4-6 ባለው ክፍል እየሰራ የነበረውን ነገር በመዘርዘር መልስ ላከለት፡፡ በሌላ አባባል ጌታ ኢየሱስ አዎን ይመጣል ተብዬ እጠበቅ የነበርኩት እኔ ነኝ፣ እነሆ መጥቻለሁ፡፡ መምጣት ብቻ ሳይሆን መሲሁ ሲመጣ ያደርጋቸዋል የተባሉ የድንቅ ስራ ማረጋገጫ ምልክቶች በመስራትና የምስራቹን ቃል በመስበክ የመሲህነት ሥራዬን በማከናወን ላይ ነኝ የሚል ነበር መልሶ የላከለት፡፡

በተለያየ ውጣውረድ ውስጥ እያለፋችሁ ያላችሁ የመድኃኒታችን ጌታ ኢየሱስ ተከታዮች እርሱ የዳናችሁበትን ወንጌል ሥራ እስከ መስቀል ሞትና ትንሳኤ ድረስ ሰርቶ ጨርሶታል፤ አሁንም ስለ እናንተ በሥራ ላይ ነው፡፡ እርሱ ስለሕዝቡ ጥቅም ይሰራል፣ በሊቀ-ካህናንነት ይማልዳል፣ በጠበቃነት ይሟገታል፤ የጠላትን ስራ እያፈረሰ ይመታል፡፡ ሕዝቡንም በእምነት ለማሳደግና ጌታውን እየመሰለ እንዲሄድ በእናንተ ውስጥ እየኖረ ይሰራል፡፡ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእያንዳንዳችን ጋር ነው፡፡ ስለዚህ ማንኛውም አማኝ በገጠመው ውጊያና በሚያልፍበት ውጣውረድ እርሱ ከጎኑ ስላለ አይደናገጥ፡፡

እነዚህ ከላይ የዘረዘራቸው ያደርጋቸው የነበሩ ነገሮች የሚመጣው መሲህ ሲመጣ የሚያደርጋቸው ምልክቶች (ማስረጃዎች/ማረጋገጫዎች) ናቸው ተብለው ከተተነበዩ ትንቢቶች ውስጥ ነበሩ፡፡

ጌታ ኢየሱስ ይመጣል ተብሎ ይጠበቅ የነበረው መሲሁ ስለመሆኑ የመሰከሩት አስረጂዎች /ምስክሮች፣ ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

1. የጻድቁ ሰምዖን ምስክርነት፡- ሉቃ 2፡25-29
2. የነብይት ሐና ምስክርነት፡- ሉቃ 2፡36-38
3. የመጥምቁ ዮሐንስ (የመጨረሻው የብሉይ ኪዳን ነብይ) ምስክርነት፡፡ ዮሐ 1፡6-8, 29-30, 32-34፤ 35-36-41፥

4. በነቢያት የተጻፉት ቅዱሳት መጻህፍትና መዝሙራት ምስክርነት የሐ 5፡38-39፣ 46-47፣ ሉቃ 24፡44፣ ሐዋ 17፡27፣ ሉቃ 24፡44፥
5. በተፈጸሙ ከ360 በላይ የሆኑ ትንቢቶች በኢየሱስ በስጋ መገለጥ መፈጸማቸው፡፡ (ከድንግል መወለዱ፣ ኢሳ 7፡14፣ ማቴ 1፡23፣ በቤተልሔም መወለዱ፣ ከኃጢአተኞች ጋር መሰቃየቱ፣ ኢሳ 53፡12፣ ሉቃ 23፡32-33፣ …)
6. የቅዱሳን መላዕክት ምስክርነት፡-
   ሀ. በመጸነሱ ጊዜ ሉቃ 30-33፣ 34-35፣ ማቴ 1፡19-21
   ለ. በተወለደ ጊዜ ሉቃ 2፡8-11፣
   ሐ. ከሙታን መነሳቱን፣ ማቴ 28፡2-7፣ (ማር 16፡5-7፣ ሉቃ 24፡4-7)
   መ. ባረገ ጊዜ፣ ሐሥ 1፡10-11 (በጠቅላላ 4 ጊዜ መስክረውለታል)፡፡

   (የክፉ መናፍስት ምስክርነት፡- ማር 1፡23-24፣ 34፤ 3፡11-12፣ 5፡1-8 (የእነርሱ ምስክርነት ለማስረጃነት መጠቀም አያስፈልግም እንጂ)
7. የሰብአሰገል ምስክርነት፤ (ጠቢባን ሰዎች ስማቸው፡- መልቸር- ከፐርሺያ፣ ጋስፐር- ከህንድ፣ ባልታዛር- ከአረብ አገር እንደ ሆኑ ይነገራል) ማቴ 2፡1-12፣
8. የእግዚአብሔር አብ ምስክርነት፣ ዮሐ 3፡13-17፣ 5፡37, ማቴ 17፡15፣
9. የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት፡- ዮሐ 15፡26፣ ሐሥ 5፡32
10. የሳምራዊቷ ሴትና የሳምራዊያን ሰዎች ምስክርነት፡- ዮሐ 4፡29፣ 39-42፣
11. "…. እንድርያስ በመጀመሪያ ያደረገው ወንድሙን ስምዖንን ፈልጎ፣ "መሲሑን አገኘነው" ብሎ መንገር ነው፤ 'መሲሕ' ማለት ክርስቶስ ማለት ነው።" ዮሐ 1፡40-41፣
12. ሲመጣ ያደርጋቸዋል ተብለው የተነገሩት ድንቅና የታምራዊ ሥራዎች ማረጋገጫ ምልክቶች መደረጋቸው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ያደርጋቸው የነበሩና አሁንም በስሙ የሚደረጉ ድንቆችና ታምራቶች ለመምጣቱ ማረጋገጫ ምልክትነት ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ የመስቀል ሞትና ትንሳኤ እያፈሰሰ ያለው ጸጋ ታላቅነት ማሳያዎችም ናቸው፡፡ (ዮሐ 5፡36፣ 6፡14፣ 25-26፣ 7፡31፣ 10፡41፣ 12፡37፣ 20፡30)፣10፡36-38፣ ሉቃ 16፡31፣ 9፡32፣ 14፡11፣ 15፡24 (ኢሳ 35፡4-6፣ 61፡1፣ ሉቃ 4፡18-19)፡፡ ዮሐ 20፡30 ላይ ጌታ በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተጻፉ አያሌ ታምራዊ ምልክቶች በደቀመዛሙርቱ ፊት ማድረጉን ይናገራል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፉት ደግሞ ከ41 ያህል ናቸው፡፡ እነዚያን ድንቅ ስራዎች ባደረገ ቁጥር እርሱ መሲሁ መሆኑን ይመሰክር ነበር ማለት ነው፡፡
13. የሐዋሪያት ምስክርነት፣ (እነርሱ የመሰከሩት አንዴ ብቻ ሳይሆን እያንዳንዳቸው ባገለገሉበት ስፍራ ሁሉና ላገኙት አዲስ ሰው ሁሉ ነው፡፡ ዮሐ 15፡27፣ 20፡21፣ 1፡40-41፣ ሐሥ 5፡41-42፣
14. የእስራኤላዊያን አድማጮች ምስክርነት፡- የሐ 4፡29፣ 6፡14፣ 7፡31፣ 40-41፣ 1ዮሐ 4፡2-3፣ 2 ዮሐ 1፡7፣
15. ተፈጥሮ ራሱ በስለቅቱ ወቅት ያሳየው ምስክርነት (እግዚአብሔር በተፈጥሮ አማካይነት ያደረገው/ የገለጠው ምስክርነት ነው) ማቴ 27፡50-53፤ (የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከታች ለሁለት ተቀደደ፣ ምድር ተናወጠች፡ አለቶች ተሰነጣጠቁ፣ መቃብሮች ተከፈቱ፣ አንቀላፍተው የነበሩ ብዙዎች ቅዱሳን ተነሱ፣ ከመቃብርም ወጥተው ታዩ፡፡)

16.የመቃብሩ ጠባቂዎች/የአገረ ገዥው ወታደሮች ምስክርነት ማቴ 27፡54፣ 28፡11-13

17.ከሙታን በመነሳቱ መቃብሩ ባዶ መሆኑ፣

18.ከትንሳኤው በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ 40 ቀን ድረስ መታየቱ ዮሐ 20፡10-13

19.በእርገቱ መሰከረ፡ ሉቃ 24፡50-53፣ ሐሥ 1፡9-11

20.የራሱ የጌታ ኢየሱስ ምስክርነት፡-, 5፡31-47፣ ዮሐ 8፥18 "ስለ ራሴ የምመሰክር አንዱ እኔ ነኝ፤ ሌላውም ምስክሬ የላከኝ አብ ነው።"

የሐ 8፡23-24 እኔ እሰርሱ ነኝ ስላችሁ ... ካላመናችሁ ...

ዮሐ 10፡23-26 አይሁድ ከበውት በጠየቁ ጊዜ፣

ዮሐ 13፡18-19፣ አልፎ እንደሚሰጥ መናገሩ፣

ዮሐ 18፡33-36-37 በጲላጦስ ፊት፣ ጌታ ኢየሱስ ከመጣበቸው ጉዳዮች አንዱ ራሱን ለሰዎች ሊያስተዋውቅ መሆኑ።

ሉቃ 24፡36-48፣ ስለ ትንሳኤው ራሱ መሰከረ፤ (ጌታ ኢየሱስ መሲሁ እኔ ነኝ የሚል ይዘት ያላቸው ምስክርነቶች በወንጌላት ውስጥ ተጽፎ ያለው ብዛት ከ30 ጊዜ በላይ ነው

ዮሐ 11፡4 ጌታ ኢየሱስ በወንጌላት ወሰጥ ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ ብሎ የጠራው 46 ጥቅሶች ውስጥ ነው። (ጠቅላላ ይህ ሐረግ በአዲስ ኪዳን የተመዘገበው ግን 72 ጥቅሶች ውስጥ ሲሆን ሐረጉ ብቻ ግን 287 ጊዜ ነው፣) እግዚአብሔር አባቴ ነው ያለው 55 ጊዜ ነው።

21.የጲላጦስ ምስክርነት፣ ማቴ 27፡17፣ 22፤

ኤልያስ ታሪኩ (ዶ/ር)        2019 ዓ.ም.